# “ቀለበቴን ስጧት እና ሌሎች መጣጥፎች”

## አዲስ የውብ መራር እንጎቻ ወጎች መድብል

ደራሲ፡ በልጅግ ዓሊ
የገጽ ብዛት፡ 192
ገምጋሚ፡ ዓለሙ ተበጀ




በልጅግ ዓሊ በዚህ መጽሐፉ ያቀረበልን ወጎች በእውን ከተከሰተ፣ አሁንም በሀገራችን እየተከሰተ ካለው መራር የሕይወት ወንዝ የተቀዱ ናቸው። የሕዝብን የዴሞክራሲና የሥልጣን ባለቤትነት ጥያቄዎች በማንሳት ከወታደራዊ አገዛዝ ጋር በተካሄደው ትግል፣ እሱም አባል የሆነበት ያ ቆራጥ ትውልድ ከከፈለው የመስዋዕትነት ገድሎች የራሱን ትውስታዎች ያወጋናል። አገዛዝን በአገዛዝ ተክቶ የሕዝብ ልጆችን ጭዳ ማድረጉን ካላቆመው የሀገራችን የዛሬ ሕይወትም እየጨለፈ ያጫውተናል።

መጽሐፉ የ15 ወጎች መድብል ነው። ለአንዱ በርዕስነት የተጠቀመበት “የሁለት ትውልዶች ወግ” የሚለው ሐረግም መድብሉ ለኢትዮጵያ ሥነ-ጽሑፍ የሚያበረክተውን ዋጋ የሚገልፀው ይመስለኛል። በዚያን ወቅት የነበርንም ሆነ ከዚያ ወዲህ የተወለዱ ወጣት አንባቢያን አብዛኞቹ ታሪኮች ከሚያወሱት ከዚያ ትውልድ ጋር በመንፈስ እንዲናወጋ ያደርገናል። የምንራመድበት የሀገራችን ምድር ትላንት በደም አበላ ተጥለቅልቃ እንደነበር፣ አሁንም ይኸው ሂደት መቀጠሉን ያስታውሰናል። ምናልባትም ሀገር ሰላም ብለን እውነታውን የምንክድ ካለን የነኝህ አዕላፍ ሰማዕታት ደም ባራሰው አፈር ላይ እንደምንራመድ ያስታውሰናል። ዛሬ ላይ ሆነን የትላንቷንም ሆነ የዛሬዋን ኢትዮጵያ ሀቅ፣ የአሁኑንም የኢትዮጵያዊያንን እንግልትና መከራ በሊቢያ፣ በሰሃራና በቤሩት እንዲናይ፣ እንዲንሰማ ያስችለናል። የዚያን ጊዜው ጭፍጨፋ ያስከተለውን የማህበራዊና ሌሎችንም ቀውሶች ግፉ በደረሰባቸው እማኞች የዛሬ ሕይወት እማኝነት ያሳየናል። ሕይወትን፣ እውነትንና ውበት አጋብቶ፣ ትላንትን ከዛሬ አቀናጅቶ፣ የሀገር ቤቱን ከባህር ማዶው ጋር አሳክቶ ውብ ታሪኮችን ያስነብበናል። እውነትና ሀሰት፣ ጽናትና ክህደት፣ ሕያውነትና ሀላፊነት፣ እኛነትና እኔነት፣ ቆራጥነትና ፈሪነት፣ ወዘተ ወዘተ ተቃራኒ ሰብዕናዎች ከሚፋለሙበት ወንዝ የተቀዱ ታሪኮች ናቸው።

እናም መራር እውነታ ናቸው - በታሪካዊነታቸው። ውቦች ናቸው - በቋንቋ አጠቃቀማቸውና በአተራረክ ስልታቸው። ሃሳቡን የማያወሳስቡ፣ አንባቢን

የማያሰለቹ አጫጭር ዐረፍተ-ነገሮችን ነው ባብዛኛው የተጠቀመው። በአንዳንዶቹም በአንድ የታሪክ ቦይ ውስጥ ብዙ ታሪኮችን አዋህዶ — ፈረንጆቹ stories within a story በሚሉት ስልት - የተዋጣለት የአተራረክ ችሎታውን አሳይቶናል። ለዚህም ከሁሉም ረዘም ያለውና "ለሞት የቀረበ" የሚለው ወጉ ጥሩ አስረጂ ነው። ክረምት ሊገባ ከሚያስገመግምበት አውሮፓ ሆኖ፣ በኮምፒውተሩ መስኮት ውስጥ "ኢሕአፓ ይወድማል! ሞት ለኢሕአፓ! … " እያለች በምታነበንበው ተናጋሪ ሰበብ በምልሰት (flashback) ቀደም ሲል ካጋጠሙት ታሪኮች ሶስቱን ያወጋናል። ታሪክ አንድ — በፖለቲካ አቋማቸው፣ በሃይማኖታቸው፣ በሃብታቸው ምክንያት ግፍ የተፈፀመባቸውን ሰማዕታት ጨምሮ የቀይ ሽብር ወቅት የእስር ቤት ሕይወት ትዝታው። ታሪክ ሁለት — በተባባሪ ወንጀለኛነት ተከሶ፣ ለመከራከርም ገንዘብ በማጣቱ ሞት የተፈረደበት የቴክሳሱ እስር ቤት የብዕር ጓደኛው። ታሪክ ሶስት — በቶሊስቶይ "ክራይም ኤንድ ፐንሽመንት" መጽሐፍ ውስጥ ሁለት ሴቶች በመግደሉ ምክንያት ሊደበቀው ባልቻለው የህሊና ፀፀት የሚጨነቀው እና ወንጀሉን አምኖ ንስሃ የሚገባው ራስኮኒኮቭ። ግን ሶስቱም ታሪኮች ትውልድ የመተረው የትላንት የቀይ ሽብር ሥቆቃ ዛሬም እንዲደገም በፓልቶክ በምትፎክረው ሴት ንግግር እና ይህ ንግግሯ በሚያስከትልበት የተራኪው ስሜት ዙሪያ ከተዋቀረው ታሪክ ጋር በጥበብ አንድ ወጥ ህብር ፈጥረዋል። እናም እነሱም ተጨምረው ሁሉም ታሪኮች አንድም አራትም ሆነው በአንድ የታሪክ ቦይ ይፈሳሉ። አንዱ ታሪክ የሌላው ማጉሊያ፣ የሌላው አካል እየሆነ፣ አራምባና ቆቦ ሳይኳኳኑ ተጋምደዋል። በአሜሪካ እስር ቤት፣ በራሻያ፣ በአዲስ አበባ የተፈፀሙ ግፎችን እያሳየ፣ በእኛው ሀገር ትላንት የፈፀሙትን ወንጀል ዛሬም ለመድገም የሚዳዱትን በፓልቶኳ ተናጋሪ ሴትዮ ወኪልነት እየታዘበ፣ ከህሊና መታረቂያው፣ ወንጀልን አምኖ፣ በእውነት ስለእውነት ንስሃ መግባት መሆኑን ያስረግጣል - ተራኪው።

በልጅግ ዓሊ በአጠቃላይ በ"ቀለበቴን ስጧት" መድብሉ ውስጥ ዛሬም የመከራ ዝናብ ያላባራባት ሀገራችንን ሕዝብ ሰቆቃ ሕይወት በጥበብ አግዝፎ እንዲናስተውል፣ እንዲናዳምጥ አስችሎናል። የዛሬው የሀገራችን መከራ የትላንት መከራዋ በቆልት ነውና መጽሐፉ ለአሁኑ ችግራችንም መፍትሄ ጠቋሚ የታሪካዊ ወጎች ስብስብ ነው። ትላንትን በእውነት ስለእውነት አውቆ፣ ዛሬን ሊታደገው ለሚሻ ጀግና አእምሮ። ለዚህም ነው አዲስ የውብ መራር እንጉቻ ወጎች መድብል ያልኩት ገና ከመነሻዬ።